የሰ/መ/ቁ. 15672
27/04/98

ዳኞች፡- 1. አቶ ከማል በድሪ
2. አቶ ፍስሐ ወርቅነህ
3. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
4. አቶ አሰግድ ጋሻው
5. አቶ መስፍን አቁበዮናስ

አመልካች፡- አቶ ታደለ ገለቻ
ተጠሪ፡- አቶ ውድመጣስ ኑሮ

*ስለ ንብረት ሽያጭ - ንብረት እንደገና በሐራጅ ስለሚሸጥበት ሁኔታ- ስለ ሐራጅ አሸናፊ ክፍያ መፈፀሚያ ወቅት - የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.442*

የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪ ባለቤት የሆነ ንብረት በሐራጅ ተሸጦ ዕዳ እንዲከፈል በማድረግ ሁለት ተጫራቾች በተለያየ ጊዜ አሸንፈው በህጉ መሠረት በ15 ቀን ውስጥ ገቢ ስላላደረጉ ድረጅቱን ባለመብቱ በንብረቱ ግምት ይረከቡት በማለት የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን ትዕዛዝ በማፅናቱ የቀረበ አቤቱታ።

**<u>ውሳኔ</u>** ፡- የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት እና ከፍተኛ ፍርድ ቤት በጉዳዩ የሰጡት ውሳኔ ተሸሯል።

1. የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 442 ላይ ንብረቱ ለምን ያህል ጊዜ በድጋሚ እንዲሸጥ በፍ/ቤቱ እንደሚታዘዝ ሳይደነግግም ንብረቱ ገዥ አያገኝም ወደሚል መደምደሚያ አያደርስም።
2. ሁለት ጊዜ ሃራጅ ሽያጭ ወጥቶ አሸናፊዎች ካልከፈሉ ለ3ኛ ጊዜ ሃራጅ ወጥቶ ቤቱ ሊሸጥ ይገባል።

የሰ/መ/ቁ. 15672

27/04 ቀን 1998 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1. አቶ ከማል በድሪ

2. አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

3. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

4. አቶ አሰግድ ጋሻው

5. አቶ መስፍን እቁበዮናስ

አመልካች፡- አቶ ታደለ ገለቻ - ታዬ ባንጃው ጠበቃ ቀርቧል፡፡

ተጠሪ፡- አቶ ውድመጣስ ኑሮ - አልቀረበም፡፡

## ው ሣ ኔ

ይህ የአፈፃፀም ክርክር ለዚህ ሰበር ችሎት ሊቀርብ የቻለው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት 1ኛ ፍትሐብሔር ቀጥታ ክስ ችሎት መጋቢት 29 ቀን 1996 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ አመልካች ቅር በመሠኘታቸው ነው፡፡

ለጉዳዩም መነሻ በሆነው በአመልካችና በተጠሪ መካከል በነበረው የአፈፃፀም ክርክር ተጠሪ (የፍርድ ባለመብት) የነበሩ ሲሆን አመልካች ደግሞ የፍርድ ባለዕዳ ነበሩ አመልካች የሚሉትም የእኔ ባለቤት ከወ/ሮ ይችዓለም ለገሠ ገዝታው ስሙ ያልተዛወረ «ሠላም የህፃናት ልብስ መደብር» የተባለው ድርጅት ተሸጦ ለዕዳዬ መክፈያ እንዲውል የፌ/ከ/ፍ/ቤት ውሣኔ ሠጥቶ የፍርድ አፈፃፀም መምሪያ ድርጅቱን አስገምቶ ፍ/ቤቱም ድርጅቱን ለሐራጅ ጨረታ እንዲቀርብ አድርጓል ሆኖም ግን ሁለት ተጫራቾች በተለያየ ጊዜ ተጫርተው ያሸነፉ ቢሆንም ሕጉ በሚፈቅደው መሠረት በ15 ቀን ጊዜ ውስጥ ገንዘቡን ገቢ ሊያደርጉ አልቻሉም በዚህም መሠረት የከ/ፍ/ቤት ቀጥታ ክስ ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 442 መሠረት ንብረቱ በጨረታ እንዲሸጥ ትዕዛዝ የሚሠጠው ለምን ያህል ጊዜ እንደሆነ የተገለፀ ነገር የለም ፣ ነገር ግን አፈፃፀሙ ተግባራዊ መሆን ስላለበት ላልተወሠነ ጊዜ ትዕዛዝ ሊሰጥ መቆየት የለበትም፣ በመሆኑም ንብረቱ ለሁለተኛ ጊዜ ተጫራች ባለመቅረቡ ምክንያት የባለዕዳውን ንብረት ባለገንዘቡ እንደሚረከበው ሁሉ ድርጅቱን ባለመብቱ በንብረቱ ግምት መሠረት ይረከቡት የሚል ትዕዛዝ ሠጥቷል፡፡

አመልካችም በዚህ ትዕዛዝ ቅር በመሠኘት ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ የጠየቁ ሲሆን ፍ/ቤቱም ጉዳዩን አይቶ የከ/ፍ/ቤት የሠጠው ትዕዛዝ ጉድለት የሌለው ነው በማለት ወስኗል።

ከዚህ በኋላ አመልካች የበታች ፍ/ቤቶች የሠጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ለዚህ ሰበር ችሎት ይግባኛቸውን አቅርበዋል። የይግባኛቸውም መሠረታዊ ነጥብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 442 ፍ/ቤቱ ንብረቱ እንደገና እንዲሸጥ ትዕዛዝ ይሰጣል ይባል እንጅ በመነሻው ግምት የፍርድ ባለመብቱ (ተጠሪ) ይረከበዋል አይልም የሚል ሲሆን ተጠሪም በዚሁ መሠረት መልሱን ይዞ የቀረበ ሲሆን አመልካችም የበኩሉን የመልስ መልስ አቅርቦ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል።

ይህ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም ጉዳዩን ከተገቢው የሕግ ድንጋጌ ጋር መርምሯል። እንደመረመረውም ክርክሩ የቀረበበትን ድርጅት ለመሸጥ ሁለት ጊዜ የሐራጅ ማስታወቂያ ወጥቶ፣ በሁለቱም ሐራጅ የሐራጁ አሸናፊዎች ሐራጁ በተደረገ በ15 ቀኖች ውስጥ የንብረቱን ዋጋ በሙሉ አልከፈሉም ተብሎ የፍርድ ባለመብቱ ማለትም ተጠሪ ንብረቱን በግምቱ እንዲረከብ መባሉ አግባብ መሆን አለመሆኑን አይቷል። በዚህም መሠረት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 442 ላይ እንደተመለከተው የጨረታ አሸናፊ የሆነው ሰው በ15 ቀን ጊዜ ውስጥ የንብርቱን ዋጋ ሳይከፍል የቀረ እንደሆነ ፍ/ቤቱ ንብረቱን እንደገና እንዲሸጥ ትዕዛዝ ይሰጣል የሚል ተመልክቷል። ምንም እንኳን እዚህ ላይ በሕጉ ውስጥ ይህ አይነት ሁኔታ የተከሠተበት ንብረት ለምን ያህል ጊዜ በድጋሚ እንዲሸጥ በፍ/ቤቱ እንደሚታዘዝ ያልተመለከተ ቢሆንም ንብረቱ ከነአካቴው ገዥ አያገኝም ወደሚል መደምደሚያ የሚያስደርስ አይሆንም። ስለሆነም በተያዘው ጉዳይ ላይ የጨረታው አሸናፊዎች ገንዘቡን አልከፈሉም ማለት ሌላ ገዥ የለም ማለት አይደለም። በዚህም መሠረት የከ/ፍ/ቤት ክርክር የተነሣበትን ድርጅት ባለመብቱ በንብረቱ ግምት መሠረት እንዲረከበት በማለት የሠጠው ትዕዛዝና የጠ/ፍ/ቤቱም የሠጠው ይህንኑ የሚያፀና ውሳኔ አግባብ አይደለም በማለት ሽረን ክርክር የተነሣበት ድርጅት በሐራጅ ይሸጥ ሲል ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ወስኗል። ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ መዝገቡ ስላለቀ ተዘግቶ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።